***መሠረት ስብሐት ለአብ፡፡ ትውፊታዊ ኀሳበ ዘመንና ታሪክ፡፡*** **አንደኛ እትም 1981 ዓ.ም. ሆንግ ኮንግ፣ ሁለተኛ እትም 2012 ዓ.ም. አዲስ አበባ፡፡ (247 ገጾች)**

**ኀሩይ አብዱ[1]**

የመሠረት ስብሐት ለአብ የምርምር *ሥራ ትውፊታዊ ኀሳበ ዘመንና ታሪክ* ከገበያ ከጠፋ ብዙ ዓመታት ያልፉታል፡፡ ከሠላሳ አንድ ዓመታት በኋላ፣ በደራሲው ቤተሰብ ጥረት መጽሐፉ ከእንደገና በመታተሙ ከአንባብያን ዘንድ ሊደርስ ችሏል፡፡ በመጽሐፉ ርዕስ የተጠቀሰው ትውፊታዊ የሚለው ቃል ‹‹ከጥንት ከአበው ሲያያዝ ሲወርድ፤ ቃል በቃል ሲነገር የመጣ›› ልማድ፣ ትምህርት፣ ወግ እና ታሪክን ይወክላል[2]፡፡ ይህም ትምህርት ደራሲው ኀሳበ ዘመን ብለው የሚጠሩት ነው፤ ሲያብራሩትም

> የዘመናትና የዓመታት የወራትና የሳምንታት የዕለታትና የሰዓታት የመሳሰለው … ጊዜያት … በኀሳብ ተመርምረው ተመዝነው ተሰፍረው ታውቀው ተቈጥረው ሲያበቁ ምድብና ቀመር ተሰጥቶኣቸው የሚገኙበት ውሳኔና ድንጋጌ እያሰማ የሚጠራበት … ባጭሩ የዘመን አቆጣጠር ድንጋጌና ውሳኔ ትምህርት ነው፡፡ (ገጽ 8)

ኀሳበ ዘመን የተባለው ጽንሰ ሐሳብ  በታሪክ ሌላ ስሞች እንዳሉት ደራሲው ይገልጻሉ፤ እነዚህም ባሕረ ሐሳብ፣ አቡሻክር፣ የቁጥር ትምህርት፣ ዘመነ ዓለም፣ እና መርሀ ዕውር ናቸው (ገጽ 8-9)፡፡ ይህ ቅኝት ጥቂት ስለ ኀሳበ ዘመን/ባሕረ ሐሳብ ካነሳ በኋላ፣ የደራሲውን የትምህርት ዝግጅት፣ የመጽሐፉን ይዘት፣ እና የምንጭ አጠቃቀም ይፈትሻል፡፡

በጥንታዊው የኢትዮጵያ ትምህርት ባሕረ ሐሳብ የሚባለው የዕውቀት ክፍል ዋና ዓላማው ከዓመት ዓመት ተንቀሳቃሽ የሆኑ በዓላትና አጽዋማት (ፋሲካ፣ ዓቢይ ጾም የመሳሰሉት) መቼ እንደሚውሉ ማስላት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መስከረም 1 መቼ እንደሚውል፣ የዕለት ሰዓታት ዕውቀት - የሰውን ጥላ በጫማ በመለካት፣ የተለያዩ አገሮች የዘመን አቆጣጠር እና የወራት ስያሜ፣ ዋና የሚባሉ ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር፣ በፀሓይና በጨረቃ ዓመታት ያሉትን የቀን፣ የሰዓታት፣ የደቂቃዎች፣ እንዲሁም የሰከንዶችን ልዩነት ማስላት የመሳሰሉትን ያስተምራል፡፡

አሁን ከተረፉን ብራናዎች መካከል የባሕረ ሐሳብን ትምህርት ሙሉውን ይዘው ከምናገኛቸው  ከቀደምቱ መሀል በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በ1374 ዓ.ም. የተዘጋጀው ብራና ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እስከ 20ኛው ምእት ዓመት የባሕረ

---

[1] ረዳት ፕሮፌሰር፣ የኢትዮጵያ ጥናት እና ምርምር ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣
ኢሜይል፡- hiruyab@gmail.com

[2] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ 1948 ዓ.ም. ገጽ 397፡፡

ሐሳብ መጽሐፎች በሰፊው መታተም እስከ ጀመሩበት ድረስ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የባሕረ ሐሳብ ብራናዎች ተዘጋጅተዋል፤ ተገልብጠዋል። ሕትመት በሰፊው በተሰራጨበት ባሁኑ ዘመንም ወደ ሀምሳ የሚደርሱ የተለያዩ የባሕረ ሐሳብ መጻሕፍት በብዙ ሺ ቅጂዎች እየታተሙ ላንባቢው ተሰራጭተዋል። የመሠረት ስብሐት ለአብ *ትውፊታዊ ኀሳበ ዘመንና ታሪክ* በሚያነሳው ሐሳብ ሆነ በምንጭ አጠቃቀም እስካሁን ከሚታተሙት መጽሐፎች ለየት ይላል።

መሠረት ስብሐት ለአብ (ሠኔ 30፣ 1914 ዓ.ም. (አክሱም) - ጥር 5፣ 1990 ዓ.ም. (አዲስ አበባ))፣ ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ትምህርት ባግባቡ የተማሩ ሊቅ ናቸው። ትምህርትን በልጅነታቸው በዜማ (የቃል ትምህርት፣ ምዕራፍ፣ ጾመ ድጓ፣ ድጓ፣ ዝማሬና መዋስዕት፣ አቋቋም) ጀምረው፣ በመቀጠል አገሪቷን እየዞሩ ቅኔ ከነአገባቡ (በተለይ ከሊቆቹ አለቃ አወቀ ዘወቂጣ እና መልአከ አርያም ይትባረክ መርሻ ዘላስታ) እና ትርጓሜ መጻሕፍትን (አንድምታ) በከፍተኛ ደረጃ ተምረዋል። ከ*ትውፊታዊ ኀሳበ ዘመንና ታሪክ* (1981 ዓ.ም.) በተጨማሪ በነገረ መለኮት እና በጥንታዊው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ትውፊት ላይ የተመሠረቱ ሌሎች አምስት መጻሕፍት አሳትመዋል። መጻሕፍቱም፣ ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ (1951 ዓ.ም.)፣ ሥረ ብዙ (1961 ዓ.ም.)፣ አርዮሳውያን (1985 ዓ.ም.) ፣ ቃል እግዚአብሔር ነበር (1987 ዓ.ም.) እና ሥላሴ በተዋሕዶ (1988 ዓ.ም.) ይባላሉ።[3]

የመሠረት ስብሐት ለአብ የጥንት ብራናዎችን የመመርመር ፍቅር ውጣኔው ገና በተማሪነታቸው ዘመን በሚማሩበት ደብር ወይም ገዳም የሚገኙትን ዕድሜ የጠገቡ ብራናዎች በማገላበጥ ነበር። ለወደፊት ምርምራቸው የሚያስፈልጋቸውን መረጃ መሰብሰብ የጀመሩት ግን በ1948 ዓ.ም. ለዐፄ ኃይለ ሥላሴ የንግሥ የብር ኢዮቤልዩ በጐንደር በተዘጋጀው የጥንት ብራናዎች ትርዒት በመገኘታቸው ነው። የቀረቡት ብራናዎች ብዛት ስለነበራቸው የተቻላቸውን ያህል ማስተዋሻ ከያዙ በኋላ የተቀሩትን ወደፊት ለማንበብ ርዕሳቸውንና የሚገኙበትን ደብር ወይም ገዳም መዝገበው አስቀመጡ። ለሚቀጥሉት ሀያ ዓመታት በዕረፍት ጊዜያቸው እነዚህን ብራናዎች ከእንደገና ለማየትና የያዙትን መረጃ ለመቅሰም አገሪቷን ሲዞሩ ቆይተዋል። ከሁሉም የበለጠ የዕውቀት ጥማቸው የተቆረጠው ግን ከ1969-1971 ዓ.ም. በእንግሊዝ አገር ቆይታቸው፣ በተለይ በዋናው ቤተ መጻሕፍት በአንድ ቦታ በመቶዎች የሚቆጠሩ ከመቅድላ የተዘረፉ ጥንታዊ ብራናዎችን ማጥናት በቻሉበት ወቅት ነበር። የእንግሊዙ ጥናታቸው ለ*ትውፊታዊ ኀሳበ ዘመንና ታሪክ* ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ደራሲው ይህን መጽሐፍ ያዘጋጁት እንግሊዝ አገር በነበሩበት ጊዜ (በ1970ዎቹ መግቢያ) ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ለቀረበላቸው የዘመን ግንዛቤ ጥያቄዎች ‹‹... ለባለ ዘመኑ ትውልድና ለሚኖሩበት አካባቢ የሚመጥን

---

[3] ከነዚህ በተጨማሪ በግዕዝ ሰዋስው እና ቅኔ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ታሪክና ባህል ላይ ተዘጋጅተው ያለቁ ወይንም እየተዘጋጁ ያሉ መጻሕፍት እንደነበሯቸው በዚሁ *ትውፊታዊ ኀሳበ ዘመንና ታሪክ* መጨረሻ ገጽ ላይ ሰፍሯል።

መልስ …›› ሊሰጡ ስለፈለጉ እንደሆነ በመግቢያቸው ያስረዳሉ፡፡ የመጽሐፉንም ዓላማ ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፤

> የኢትዮጵያ ኀሳበ ዘመን ወይም ባሕረ ኀሳብ ዘመነ ዓለም ወይም የዘመን አቆጣጠር እንዴት እንደሆነና በሀገሪቱ እንዴት እንደተገኘ እንደምንስ ባለው ሁናቴና ይዞታ ተጠብቆ እንደሚገኝ በታሪክ መልክ ተገልጾ በዚሁ ጽሑፍ ቀርቦአል (ገጽ 8)

መጽሐፉ ሦስት ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ እነዚህም 1) የኢትዮጵያ ኀሳበ ዘመን (ባሕረ ኀሳብ) ከየት መጣ (ገጽ 8 — 45)፣ 2) የኢትዮጵያ ዓመተ ዓለም አቆጣጠር እንዴት ተገኘ (ገጽ 46 — 172)፣ 3) ባሕረ ኀሳብና አገባቡ - የጊዜ መስፈርት ጽንሰ ሐሳቦች (ገጽ 173 — 232) ናቸው፡፡

ክፍል አንድ የሚጀምረው ለዘመን አቆጣጠር የሚሰጡትን የተለያዩ ስሞች ብያኔ በመስጠት ነው፡፡ በመቀጠል ደራሲው ከሳቸው በፊት ስለ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አመጣጥ የተጻፉ ሥራዎች ምን ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፤ የቀደሙትም ደራስያን ‹‹..የኢትዮጵያ ኀሳበ ዘመን አወጣጥ ከፋርስ፣ ከእሥራኤል፣ ከእስክንድርያ … ›› (ገጽ 11) መጣ ብለው እንደሚያምኑ ይጠቁማሉ፡፡ መሠረት ስብሐት ለአብ ዕውቀት እና ጥናት ሊያድግ የሚችለው ከዚህ በፊት የተሰሩ ስራዎችን በተገቢው በመመርምር ጥንካሬያቸውንና ጉድለታቸውን በማውጣት እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን የከየትመጣ መላምቶች አንድ በአንድ በመፈተሽ፣ የትኞቹ በመረጃ ሊደገፉ እንደሚችሉ የትኞቹ ደግሞ ያለምንም ምስክር እንደቀረቡ ካሳዩ በኂላ ውሳኔውን ለአንባቢው ይተዋሉ፡፡ የደራሲውም የዚህ ክፍል ግኝት የሚነግረን፣ የኢትዮጵያ ባሕረ ሐሳብ የራሱ የሆኑ የዘመን አቆጣጠር መሠረታዊ ሀሳቦችን ይዞ የጀመረና በጊዜ ሂደትም የተለያዩ የውጪ ሀሳቦችን ተበድሮ የራሱ እንዳደረጋቸው ነው፡፡

በሁለተኛው ክፍል ደራሲው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሰነዶች እንደ ዘመን መቍጠርያ ሆኖ ሲያገለግል የቆየውን ዓመተ ዓለም ላይ ሰፊ ምርምር አድርገዋል፡ ፡ ዓመተ ዓለም ማለት አሁን የምንጠቀምበት ዓመተ ምሕረት ላይ 5500 ዓመታት በመደመር የሚገኘው አቆጣጠር ነው፡፡ ለምሳሌ ዘንድሮ በዓመተ ዓለም ስንት ይሆናል ብንል 2015 ላይ 5500 እንደምራለን - ይህም 7515 ዓመተ ዓለም ያስገኛል፡፡ ይህ አቆጣጠር በአብራሃማዊ ሃይማኖቶች የመጀመርያው የሚባለው ሰው (አዳም) ከተፈጠረ እስካሁን ያለፉትን ዓመታት ይቆጥራል፡፡ በመነሻው ዓመት ላይ ስምምነት ስለሌለ አይሁዶች አሁን ያለንበት 5783 ዓመተ ዓለም ነው ሲሉ፣ ምዕራባውያን ደግሞ 5974 ዓመተ ዓለም፣ ኢትየጵያውያን ደግሞ ከላይ እንደተጠቀሰው 7515 ዓመተ ዓለም ነው ይላሉ፡፡ መሠረት ስብሐት ለአብም ይህን መነሻ ይዘው የተለያዩ ብራናዎችን በሰፊው በመመርመር እነዚህ 5500 ዓመታት (ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት የተቆጠሩት ዓመታት የሚባሉት) እንዴት በኢትዮጵያውያን እንደተሰሉ አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በፊትም ቀደምት ሊቃውንት ይህ

አቆጣጠር ከሌሎች አገሮች የተለየበት ምክንያት የተለያዩ የኦሪት መጻሕፍት ግልባጮች ስላሉ ነው ብለዋል፡፡[4]

ሦስተኛው ክፍል በሁሉም ዘንድ በተለምዶ ባሕረ ሐሳብ ተብሎ የሚጠራውን ትምህርት ያቀርባል፤ የዚህም ይዘት ከላይ ተዘርዝሯል፡፡ በመጨረሻም ደራሲው ከተለመደው መንገድ ተለይተው የዘመን አቆጣጠር በታሪክ ሂደት እንዴት እንደሚቀያየር ለማሳየት አንድ ምዕራፍ አዘጋጅተዋል፡፡ የምዕራፉም ርዕስ፣ ‹የድሮ የኅሳበ ዘመን ሊቃውንት አንድ ደርጊት የተፈጸመበትን ታሪካዊ ጊዜ ሲያሳዩ እንዴት ያለ የአመዘጋገብ ይዞታ ነበራቸው (ምዕራፍ 33)› ይዘቱን በሚገባ ይገልጻል፡፡ ሐሳባቸውን ለማብራራት ሦስት የዘመን አቆጣጠር የያዙ ብራናዎችን አቅርበዋል፣ እነዚህም የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መጽሐፈ ምሥጢር (1416 ዓ.ም.)፣ ገድለ በረላም (1545 ዓ.ም.)፣ እና መጽሐፈ ሐዊ (1574 ዓ.ም.) ናቸው፡፡

*መሠረት ስብሐት ለአብ* ስለ ምንጭ አጠቃቀምና አመራረጥ ያላቸው አስተያየት በጣም የዳበረ ነው፡፡ በመጽሐፉ መጨረሻም 46 ብራናዎች፣ 22 በሀገር ውስጥና በውጭ የታተሙ የግእዝ መጻሕፍት፣ 34 በአማርኛ የተጻፉ የምርምር ሥራዎች፣ እንዲሁም 10 በእጃቸው የሚገኙ ያልታተሙ የሰዋስውና የሐተታ ምዕላዶች እንደ ምንጭ ተዘረዝረዋል፡፡ ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ የሚለውን አባባል በመከተል ምርምር ሲደረግ ከዋናው ምንጮች መነሳት እንደሚያስፈልግ ያትታሉ፡፡ ደራሲው እንደሚሉት፣ ‹‹ *ቀዋምያን መተርጉማን ውሳኔያዊ አባባል ‹ቅርንጫፍ ከሥር ይመጣል --- እንጂ ሥር ከቅርንጫፍ እንደማይወጣ› ምንግዜም መመሪያችን ነው (ገጽ 234)››* ፡፡ እነዚህም ‹ሥራዊ› ምንጮች የሚሏቸው መጽሐፍ ቅዱስና በግዕዝና በአማርኛ የተዘጋጁ የሊቃውንት የሥነ ኅሳብ ሥራዎችን ያካትታሉ፡፡

እንደደራሲው አስተያየት መመርመር ያለበት ዋናው ሥራ(ምንጭ) እንጂ በጽሑፉ ላይ የተሰራ ሐተታዊ ድርሰት አይደለም፡፡ ይህን መርሆ ለማሳካት እንግሊዝ አገር ሳሉ ከመቅደላ የተዘረፉትን የዘመን አቆጣጠር ብራናዎች በሰፊው መርምረዋል፡፡ በመጽሐፋቸው መውጫም እነዚህን ብራናዎች ዘርዝረዋል፤ ከረጅሙ ባጭሩ ለመጥቀስ - ሐሳበ ርቱዕ፣ መቅድመ ሐሳብ፣ መጽሐፈ አቡሻክር (ሦስት የተለያዩ ብራናዎች)፣ ሐሳበ ድሜጥሮስ፣ ዮሐንስ መደብር፣ ሚጠተ ብርሃናተ ሰማይ፣ ዜና አርዕስተ ሐሳብ የመሳሰሉት ይገኛሉ፡፡

በብራና ላይ ተዘጋጅተው የተጻፉ ድርሳናት እንደ ምንጭ መጥቀስ ከተፈለገ ማውጫ ካልተዘጋጀላቸው ወይንም የገጽ ቁጥር ካልተሰጣቸው ለመጥቀስ ማስቸገራቸውን ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም ብራናዎች ወጥ የሆነ የቃላት አጠቃቀም እንደሌላቸው ሲገልጹ፣ ‹‹የአንዳንድ ፣መጻሕፍት የአርእስት አከፋፈል በምዕራፍ

---

[4]*መምህር* ክፍለ ጊዮርጊስ፡፡ *መርሐ ዕዉር*፣ 1889 ዓ.ም. አሳታሚ Ignazio Guidi (1896), Il Marha Ewur, *Rendiconti della Reale Accademia dei Lincei*, Serie 5, Volume 5, 363-385. አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ፡፡ *መጽሔተ አሚን*፣ 1946 ዓ.ም. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡ ገጽ 17፡፡

ሲመደብ የሌሎች ደግሞ በአንቀጽ ወይም በክፍል ወይም በቁጥር ተመድበው ይገኛሉ››። ማውጫ ለተዘጋጀለት ብራና ግን (ለምሳሌ እሳቸው የተጠቀሙባቸው በእንግሊዝ ቤተ መጻሕፍት የሚገኙ ብራናዎች) ‹‹የገጹን ቁጥር … በአንዳንድ አሻሚ ቦታ የዓምድና የመሥመር ቁጥር ለማቅረብ ተገደናል›› ይላሉ። በሚያሳዝን ሁኔታ በተሰጣቸው አላግባብ የዘመናዊ ጥናት ምክር ትውፊታዊውን የቃል ማስረጃ አስቀርተዋል - ‹‹ከልዩ ልዩ መምህራንና ሊቃውንት ቃል በቃል የሰማሁትን ለማስረጃነት ባቀርበው እወድ ነበር። ነገር ግን ‹በጽሑፍ የተጨበጠ መሆን አለበት ስለሚባል እያዘንሁ አቆይቼዋለሁ (ገጽ 238)››

መሠረት ሰብሐት ለአብ በሀገራቸው ዕውቀት የሚኮሩ ናቸው፤ ይህ ማለት ግን ‹ኢትዮጵያ ሁሉም ነገር አላት፣ ከሁሉም ትበልጣለች› የሚል ጭፍን ተዐብዮ አይደለም። ኢትዮጵያ ሁሉም ነገር ባይኖራትም ያላትን ግን በሚገባ መርምረው በቂ ሆኖ መገኘቱን ከማወቃቸው የተነሳ የመነጨ ኩራት ነው። ይህንንም የኮሩበትን የቀደምት ሊቃውንት ጥናት ለሚቀጥሉት ትውልዶች እንዲደርስ በአቅማቸው በቀለለ መንገድ ለማስረዳት ሞክረዋል። ያለተቋም እርዳታ ይህንን በሙላ መስራታቸው የሚገርም ነው። ሥራቸውን የሚያኸዝብ የሚያሠራጭ ባለመኖሩ እስካሁን የሚገባውን ያህል አልተነበበም።[5] አገራዊው ዕውቀት ላይ የሚደረገው ጥናት እንዲጠነክር፣ ከዚህ በፊት በሰፊው የተመራመሩ ምሁራኖች ባይመሰገኑም ቢያንስ ስራቸው ተነቦ ከዚያም ምን ተጨማሪ አዲስ ምርምር እንደሚያስፈልግ መወጠን ይቻላል። በመጨረሻም መሠረት ስብሐት ለአብ ስለ ሥራቸው በተናገሩት ለመደምደም፤

> ምንም እንኳ ሥርጋዌ ቃላት (በቃላት ያሸበረቀ ውበት) ባይኖረውም፣ አባቶቻችን ጊዜያቸውን ሠውተው ታሪኩን መዝግበውልን በተገኙ መጻሕፍት ምንጭ፣ ባህላዊ አብነቱን በማገናዘብና ማስረጃን በማቅረብ ጽሑፉን ሳጠናቅቅ ባለችኝ ዐቅም መጠን የደከምሁበት መሆኑን በመረዳት የአንባብያን ዓይነ ልቡና ያተኩርበት ይሆናል የማለት ተስፋ አለኝ።(ገጽ 4)

[5] ለሚቀጥሉት እትሞች የደራሲው የሕይወት ታሪክ እና የመጽሐፉ አውዳዊ መግለጫ እንደ መግቢያ ቢጨመሩ መጽሐፉን እና ደራሲውን ለአዳዲስ አንባብያን ጥሩ ያስተዋውቃል።

**Book Review Summary**

Author: Mäsärät Səbhat lä’b
Title: Təwfitawi Ḥasabä Zämänəna Tariku (Traditional Ethiopian Computus and its History)
Publisher: The Author’s Family
Date: First Edition 1981 Ethiopian Calendar (1988); Second Edition 2012 Ethiopian Calendar (2020)

Reviewer: Hiruy Abdu

The author, a traditional scholar, spent decades collecting manuscript sources for his research on this book. The work is divided into three parts: part 1 delves into the origins of the Ethiopian system of computus; part 2, the longest section of the book, demonstrates the derivation of the Ethiopian ‘amätä ‘aläm calendar (*anno mundi*); part 3 deals with the basics of bahərä Ḥasab and the concepts of time units.